# “አዲሱን ወይን በአሮጌው አቁማዳ” የማይቻል ፖለቲካ

ክፍል ሁለት

**ዮናስ 12-24-14**

ጉዳያችን ምርጫ 2007ን ታሳቢ አድርጎ ስለሚካሄድ አዲሱን ወይን በአሮጌው አቁማዳ የመጨመር ሙከራና የማይቻልባቸውን ሚስጥራቶች መተረክ ነው፡፡ ትርክታችንን በክፍል አንድ በተመለከተው አግባብ በአጠቃላይ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱ ከመርህም ሆነ ከተጫባጭ ውጤት፤ ሃገራችን ያለችበትን ደረጃ የፈተሸ እና አሁንም ሊፈታ ያልቻለውን እና አዲሱን ወይን በአሮጌው አቁማዳ የመጨመር የከሸፈ ሙከራ ካሳለፍናቸው 2 ሃገር አቀፍ ምርጫዎች (97 እና2002) አኳያ እያንሰላሰልን ያጠየቅንበት ነው፡፡ የመጀመሪያውን ክፍል ስንቋጭ ባወሳነው አግባብ በክፍል አንድ የተመለከቱ የመርህም ሆነ የተጨባጭ ዴሞክራሲያዊ ጉዳዮች መነሻ አድርገን ትዝታችንንም እየጨለፍን ሰሞነኛ የሆነውን እና በሰለማዊ ሰልፍ ስም የተቀነባበረን ሴራ በዚህ ክፍል ለመኮምኮም መነሻችን የሰላማዊ ሰልፎቹን መነሻና መድረሻ በተመለከተ የሰፈሩ ሰሞንኛ ዘገባዎችን መጀመሪያ በመመልከት እና የተጠየቀ ጥያቄዎች በማንሳት ነው፡፡ ከዚያም ይህን በሰላማዊ ሰልፍ ስም የተቀነባበረ ሴራ ዓላማ አዲሱን ወይን በአሮጌው አቁማዳ ለመጨመር የሚደረግና አስቀድሞ የተጀመረ በተለይም በክፍል አንድ የተመለከቱትና የከሸፉት ሙከራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምርጫ 2007ን ታሳቢ በማድረግ ከዛሬ 2 እና 3 ዓመታት በኋላ መጀመሩን ተጨባጭ አስረጂዎች እያቀረብን እንሞግታለን፡፡

ከሙግታችንም ተነስተን የሴራዉን መድረሻ በክፍል 3 እና በመጨረሻው ክፍል ትርክታችን እናመለክታለን፡፡ ስለሆነም በክፍል አንድ በተመለከተው አግባብ በመርህም ሆነ በተጨባጭ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታችን ያለበት ደረጃ ረጅም ርቀት ላይ ቢሆንም አሁንም ህግንና ህገወጥነትን በማጣቀስ ሥርዓቱን ለመቀልበስ የሚተጉት ኃይሎች ፈተና መሆናቸው እየታየ ነውና አነሳሱን ወደኋላ 2 ዓመት ተመልሰን ከመመልከታችን በፊት ሰሞነኛ የሆነውን በሰላማዊ ሰልፍ የተቀናበረውን ሴራ እና ሴራውን ተከትሎ እየተራገበ ያለውን ጸረ ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ መጀመሪያ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

የነገሬ መነሻ ሰሞኑን ህገወጥ የሆነ አዳር ሰልፍ ባልተፈቀደና ልማት በሚከናወንበት ቦታ ላይ የጠራው ‹‹የዘጠኙ ፓርቲዎች›› ስብስብ ቢሆንም ይህንና ህገወጥ የሆነ (በምርጫ ቦርድ እውቅና ያልተሰጠው) ስብስብ የሚመራውና ቁንጮ ሆኖ የሚያጋፍረው ሰማያዊ የተሰኘው ፓርቲ ነው፡፡ ይህ ፓርቲ የተጠራውን ህገወጥ ሰልፍና የተወሰደውን እርምጃ ተከትሎ የኒዮ ሊበራል ሃይሉና የማጋፈር ፖለቲካው ስብስብ አብደው ያሳበዱንን ዘገባዎች ከመመልከታቸን በፊት አብደው ከሚያሳብዱቱ እና ፖለቲካን በማጋፈር ጨዋታ ውስጥ ገብቶ የተወሰደውን እርምጃ ካወገዙቱ መካከል ግንባር ቀደም የሆነው አንድነት በልሳኑ ፍኖተ ነጻነት በኩል ስለሰማያዊ ፓርቲ ያሰፈረውን ነጥብና አስቀድመን እኛም ስንል የነበረውን እውነታ ከዚህ ጋር ብንጠቅሰው ርዕሰ ጉዳያችንን ምሉዕ ያደርገዋል፡፡

የተቃውሞውን ፖለቲካ በሚፈትሸው ፍኖተ ነጻነት ትርክት አንድነት ተንቆለጳጵሶ የሌሎቹ ገመና መገለጡ በራሱ የተቃውሞውን ስብስብ የሴራ ፖለቲካ ቢያመላክትም አንድነትን ጨምሮ ሁሉም የሚገልጡትን የከሰረ ፖለቲካ እንደየአግባቡ ከዚህችው ጋዜጣ ላይ ወስደን የምናይ ቢሆንም ትርክታችን አሁን ላለበት ደረጃ ከፍተኛው ቀንጭበን የምናየው ‹‹ሠማያዊ እንደ ናርሲስስ›› በሚል ርዕስ ስር የተመለከተውን እና ሰማያዊ ፓርቲን የሚያጠይቀውን ነው፡፡ እንዲህ ይላል ፡-

‹‹በግሪክ አፈታሪክ (ሚዝ)፣ ውስጥ ለናርሲሰስ አጉል አወዳደቅ መንስኤው በራሱ ፍቅር መጠለፉ መሆኑ ይተረካል፡፡ ይህ ተረት ቀመስ ግለሳባዊ ተአብዮ በህያው ፓርቲ ህልውና ውስጥም እያየነው እንገኛለን፡፡ ግብታዊ እርምጃ ባልተዘጋጁበት ቀጠና ዘው ብሎ መግባትና የእርምጃውን ፍጥነት ራሱ አለመውሰዱ ፤የታቀደና የተጠና የትግል ስልት ይቅርና ጥራት ያለው ዘመኑን የሚዋጅ የፖለቲካ ፕሮግራም አለመኖሩ ፤ በአመራር አካባቢ የሚታየው ልሂቃን ድርቅና ፤ለራስ የሚሰጥ የተጋነነ ግምት ከጅምሩ ለድርጅቱ የነበረው ተስፋ እንዲደበዝዝ አድርጎታል፡፡ በተለይም በከተማ ተንጠልጥሎ የቀረው አደረጃጀቱ እና በቂ ህብረ ብሄራዊ ስብጥር አለመያዝ ፣ ፓርቲውን አንድ ጠንካራ ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ እንዲመስል እንጂ ለ‹‹ፖለቲካ ፓርቲነት ›› ብየና የሚያስቸግር አድርጎታል፡፡

ይህን የሠማያዊ ፓርቲ መገለጫ ያሰፈረችልን የአንድነቷ ፊኖተ ነጻነት ይህን እውነት በባለቤቷ አንድነት በኩል ነግራን ስታበቃ የሰማያዊን ዘው ብሎ የተገባ ሰልፍና ግባታዊ እርምጃ ተከትሎ የተወሰደውን እርምጃ ለማውገዝም አንድነት አንደኛ መሆኑ ጥቅም በሌለው የዱልኝታ ፖለቲካ መነከሩን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩልም የኒዮ ሊበራሉ ሃይል ሰለባ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

አንድነቱ ብቻ ሳይሆን ሁሉም በሚያሰኝ ሁኔታ ለግብታዊው ሰልፍ የተሰጠውን መልስ በክፍል አንድ ትርክታቸን በተመለከተው የ97ቱ እና 2002ቱ ትዝታችን አግባብ ፓርቲዎቹ እና ኒዮ ሊበራል ሚዲያው እንዴት እንደተቀባበሉት ደግሞ እንመልከት፡፡

“በ2007 ዓ.ም ግንቦት ሊካሄድ ለታቀደው ብሔራዊ ምርጫ አስቀድሞ ፖለቲካዊ ተቃውሞዎች በመላ ሀገሪቱ ሊካሄዱ እንደሚችሉ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ የአሜሪካ ዜጎችን ሊያሳስብ ይወዳል” ሲል አስቀድሞ ለቀለም አብዮት የወጠነውን ሴራ የተመለከተ መግለጫ ከአሜሪካ ሬዲዮ ዘገባ የሰማነው ሰሞኑን ነው። እነዚህ የተቃውሞ ሰልፎች በፖለቲካ ፓርቲዎች እና ቡድኖች በሀገሪቱ ዙሪያ በግልጽ አደባባዮች ሊካሄዱ እንደሚችሉ መጠቆሙንም አስደምጦናል።

በሰላም ለመከናወን የታቀዱ የተቃውሞው ሰልፎች ብጥብጥ እና ግጭት ሊነሳባቸው እንደሚችል በመጥቀስ ኤምባሲው የአሜሪካ ዜጎችን አሳስቧል ያለው ዘገባው የአሜሪካ ዜጎች ተቃውሞ ሰልፍ በሚካሄድባቸው ወይም ሕዝብ በብዛት በተሰበሰበባቸው አካባቢዎች ለደህንነታቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማስጠንቀቁን አስታውቋል።

የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ኃላፊ አቶ ዳንኤል በቀለ፣ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ቀንን በማስመልከት በአፍሪካ እና በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ላይ የወጣውን ሪፖርት በማስመልከት የሰጡትን ቃለ ምልልስም አስደምጧል።

ኢትዮጵያን በሚመለከት በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በልማት ሥራዎች ደስ የሚል ውጤት እየታየ ቢሆንም በሰብዓዊ መብት አያያዝ ረገድ አሳሳቢ ነው ሲሉ የገለጹት አቶ ዳንኤል

በጋዜጠኞች፣ በፖለቲካ ተቃዋሚዎች እና ደጋፊዎች ናቸው ተብለው በሚታሰቡ ሰዎች፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ግለሰቦች በርካታዎቹ በእስር ላይ እንዳሉ ይታወቃል ማለታቸውንም ከቃለ ምልልሱ አድምጠናል።

ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ ሁኔታ እየጠበበ እና እየተዘጋ የሄደበት ገጽታ ነው ያለው ያሉት አቶ ዳንኤል የሲቪል ማኅበረሰብን ለማስተዳደር የወጣው እና የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ ሥራ ላይ መዋል፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያዘጋጁት ሰልፍ መታገድ አሳሳቢ የሰብዓዊ መበት ጥሰቶች ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።
ሌላኛው አክራሪ የሆነው የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ የኢትዮጵያ መንግሥት በዜነቹ ላይ የሚፈፅመው የመብት ረገጣ እየተባባሰ ነው ሲሉ በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሂዩማን ራይትስ ዎች የምሥራቅ አፍሪካ ምክትል ኃላፊ ሌስሊ ሌፍኮው መናገራቸውን አስደምጧል።

“የኢትዮጵያ የሰብአዓዊ መብት ይዞታ ባሁኑ ወቅት በጣም አሳሳቢ ይመስለኛል ሲሉ የተደመጡት ኃላፊው እንደሚመስለኝ ባለፉት 10 ዓመታት በመገናኝ ዘዴዎች፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚሠሩ መያዶች፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ይሁን በሌሎች ነፃ ድምፆች ላይ የሚፈፀመው ጥሰት ያለማቋረጥ እየባሰ ነው ሲሉ የገለጹለት መሆኑንም አስደምጦናል።

በርካታና አክራሪ የሆኑ መገናኛ ብዙሃኖች ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ የዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር የጠራው የአደባባይ ስብሰባ እና ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት ታጣቂዎች መበተኑ እና ለተቃውሞ በወጡ የፓርቲዎቹ አባላትና አመራሮች መታሰራቸውን እንዲሁም ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ዘግበዋል።

የጀርመን ድምፅ ሬድዮ አዲስ አበባ ለሰላማዊ ሰልፍ አደባባይ የወጡ ሰላማዊ ነዋሪዎቿ፣ ነዋሪዎቿን ለሰላማዊ ሰልፍ የጠሩ የሰላማዊ ትግል አቀንቃኝ ፖለቲከኞቿ በፖሊስ ቆመጥ ተቀጠቀጡ፤ ተፈነከቱ፤ ተሰባበሩ ሲል ነው ያስደመጠን።

የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮም በተመሳሳይ “መድረክ በሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች እና ደጋፊዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ ይቃወማል ሲሉ የፓርቲው የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር መረራ ጉዲና መናገራቸውን በዘገባው አስደምጧል።

በዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር አማካይነት ሊካሄድ የነበረው የአደባባይ የአዳር ሰልፍ ለመበተን ፖሊስ የወሰደውን የኃይል እርምጃ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ማውገዙን ደግሞ ያስነበበን ሰንደቅ ጋዜጣ ነው።

Amnesty International የተባለውና በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም ለቀለም አብዮት ሲተጋ በተደጋጋሚ የሚገኘው ተቋም በድረገጹ ከዘጠኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ የሞከሩ 90 የሚሆኑ ሰዎች እና የፓርቲዎቹ አመራሮች መታሰራቸውን ገልጾ እስራቱ የሚያሳየው መንግሥት ከመጪው ምርጫ አስቀድሞ በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ እየሰነዘረ ያለው ጥቃት ነው ሲል ተችቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በሰላማዊ ሰልፉ የተሳተፉትን እንዲሁም የፖለቲካ አቋማቸውን በመግለጻቸው ምክንያት የታሰሩትን ሰዎች ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊለቅ ይገባል ሲል ያሳሰበው ድርጅቱ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ከመጪው ምርጫ ቀደም ብሎ በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት ተባብሶ ይቀጥላል የሚል ስጋት አለው ሲልም ገልጿል። እነዚህ ወዘተ የሆኑ ዘገባዎችና መግለጫዎች የቀለም አብዮቱን ህልመኞች የተሳሰረ ክንድ ለማጠየቅ የሚረዱን ይሆናሉ።

በአንድ በኩል ከፍኖተ ነጻነት ላይ በወሰድነው አስረጅ የብሄር ስብጥር አስፈላጊነትን እንደሚቀበለው የተመከተው አንድነት ዋና ብሄርተኛ ስለመሆኑ ሰማያዊ መኢአድ ይሁን መድረኩ በክፍል አንድ በተመለከተው አግባብና ከኢትዮ ምህዳር ላይ ወስደን እንደማሳያ ባሰፈርነው አስረጅ ያለፈውን መንገድ እየተከተሉ ስለመሆናቸው በተለይ ምርጫ 2007ን ታሳቢ ያደረጉ የ2 ዓመታት መንገዶችን ደግሞ እዚህ ጋር መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በአገራችን የትምክህት አስተሳሰብ ዋነኛ አራማጅ የነበረው የደርግ መንግስት በህዝቦች ትግል ከተገረሰሰ በኋላ በስልጣን ላይ ሆኖ ሃገሪቱን የሚያምስና የሚያተራምስ የትምክህትና የጥበት ሃይል የለም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሥርዓቱም ሆነ የሚመራባቸው ህጎችና በተግባር ላይ ያዋላቸው መርሆዎች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ እኩልነትና በዚህ ላይ የተመሰረተ የህዝቦች አንድነትን ለመገንባት ያስቻሉ በመሆናቸው ነው፡፡ይህ መሰረታዊ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ሥርዓቱን ለማፍረስ በፖለቲካ ፓርቲ ስምና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ስም የሚንቀሳቀሱ የትምክህትና ጠባብነት ሃይሎች በጋራ በመቀናጀትም ሆነ በተናጥል መኖራቸውን አለማመን አይደለም፡፡ እነዚህን ለመለየት እና አስረግጠን የመኖራቸውን ጉዳይ ማጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡የትምክህት አስተሳሰብ መገለጫ ብዙ ቢሆንም ዋነኛ ይዘቱና አላማው ግን የአንድን ወገን በላይነትና የሌላውን ወገን የበታችነት ማስፈን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህንና ከ1983 በፊት የነበረ እውነታ የትምክህት አስተሳሰብ የተጸናወተው ሃይል ሥርዓቱ የፈጠረለትን የመደራጀት መብትና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ተጠቅሞ ይህንኑ ያጎናጸፈውን ሥርዓት በማፍረስ በቀድሞ ገዥ መደቦች ወይም የእነርሱን ፈለግ በሚከተሉ ክፍሎች የበላይነትና በምልአተ ህዝቡ የበታችነት መተካት አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

አገራችን ከ23 ዓመታት በላይ የዲሞክራሲያዊ እኩልነትና ህዝባዊ አንድንትን አቅጣጫ ተከትላ በመገንባቷ ይህ ህልም እውን ሊሆን አይችልም ተብሎ ቢታመንምና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በምርጫ 97ቱ የተወገደ ቢመስልም በምርጫ 2002 ብልጭ ብሎ አሁን ደግሞ በደንብ መስፋፋቱን ግን መካድ አይቻልም፡፡

መካድ የማንችለው ደግሞ ካለፉት 23 ዓመታት ጀምሮ ብልጭ ድርግም እያለ አሁን ደግሞ በስፋት እየተገለጠ መሆኑን የሚያመላክቱ በቂና የበዙ አስረጂዎች ስላሉ ነው፡፡ይህ ሃይል በስሙ የፖለቲካ ፓርቲና የግል ሚዲያ ቢሆንም በተግባር ግን በዚሁ ስሙ እየተጠቀመ የትናንቷ ኢትዮጵያ ከዛሬዋ ኢትዮጵያ በእጅጉ የተሻለች እንደሆነች አድርጎ በማቅረብ የምናውቀውና የሚገለጠው ነው፡፡ፍጹም ጸረ ዴሞክራሲያዊ የነበረውን ዘውዳዊ አገዛዝ በማቆነጃጀትም የሚታወቅ ስብስብ ነው፡፡

ከአጼ ሚኒልክ እስከ አጼ ሃይለ ስላሴ የነበሩትን ዘውዳዊ አገዛዞች ግፍና በደል ሸፋፍኖ የስልጣኔና እድገት አባቶች አስመስሎ የሚያቀርባቸው ሃይል ማነው? ቢባል መልሱ ግልጽ ይሆናል፡፡ በዘፈን በስነጽሁፍና በልዩ ልዩ ስልቶቸች መደገፉ ሳያንሰው በአጼ ሚኒልክ በደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦችና በኦሮሚያና ሐረሪ ህዝቦች ላይ የተፈጸሙትን ጭፍጨፋዎችና የመሬት ንጥቂያ የተቀደሰ ጦርነት አስመስሎ እስከ ማቅረብ የደረሰና ይህንንም በአደባባይ የሚገልጠው ሃይል ማነው ቢባል? መልሱ ብዙም የሚከብድ አይሆንም፡፡ የደርግ መንግስት በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን እንዳልጨፈጨፈ ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአርሶ አደርና የድሃ ከተማ ነዋሪዎችን ልጆች እያሰገደደ ወደ ጦርነት እንዳልማገደ ፣ የግልና የቡድን መብቶችንም እንዳላዳፈነ ለኢትዮጵያ ዋነኛ ጠበቃ የነበረ አስመስሎ የሚያቀርበውም ማነው? ቢባል አሁንም ግልጽና ቀላል መልስ ማግኘት አይከብደንም፡፡ ለዚህ ምላሽ ደግሞ በድፍኑ ሳይሆን አንድ ጥያቄ በማንሳት የምላሹን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የመድረኩ አባል ሆኖ (የመድረኩ የሚበዙ አባል ፓርቲዎች ከኦሮሚያና ደቡብ ህዝቦች መሆናቸው ይታወቃል) ጊዜ ከገዛ በኋላ አስቀድሞም የመድረኩ አባል መሆንን ከትምክህት አስተሳሰቡና በስም ህብረ ብሄራዊ ሆኖ ስለ አንድ ብሄረሰብ ከሚያቀነቅነው መኢአድ ጋር በፍቅር ወድቆ ግን ፍቅሩን ያልጨረሰው አንድነት ስለምን ከመድረኩ ወጥቶ ከመኢአድ ለመዋሃድ አሰኘው ?። ከመድረኩ ለመውጣት ያቀረባቸውን ምክንያቶች ስናስታውስ መልሱ ግልጽ የሆነ ይመስላል፡፡ በስም የግል ሚዲያ የሆኑትንና ሚኒሊክን ሲያንቆለጳጵሱ ደርጉን በማጀገን የብሄር ብሄረሰቦችን መብትም ‹‹እስከመጨፈር›› ፋይዳ የሰጡትን ጋዜጦችም ስናሰታውስ በግልጽ የትኛው ስብስብ የትምክህት ሃይል ፍላጎቱን በፓርቲና በግል ሚዲያ ስም ለማሳካት መፍጨርጨሩን ለመገንዘብ ያስችለናል፡፡

በስም ህብረ ብሄራዊ መስለው ሌሎቹን ብሄርተኛ የሚሉትንና ነገ ደግሞ የባሱቱ ጠባብ ብሄርተኛ መሆናቸው በትምክህት አስተሳሰባቸውና መገለጫቸው ያሳዩትን መኢአድና አንድነት የተሰኙ ፓርቲዎችን በተጨባጭ አስረጅ በመመልከት ጉዳያችንን እያጠናከርን እንሂድ፡፡

መላ የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብታቸው የተከበረበትን ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት በጥብቅ አክበረው ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ለመጡ ወንድምና እህቶች መልካም አያያዝ እንዳላቸው የሚታወቅ ነው፡፡ በኦሮሚያ በደቡብ ኢትዮጵያ ፣ በጋምቤላ

ቤኒሻንጉል ሱማሌ ሐረሪ ብሄርንና ማንነትን መለያ ሳያደርግ ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ከመጡ ወገኖቹ ጋር በፍቅርና በእኩልነት የሚኖር መሆኑም የማካድና በተግባር የሚታይ እውነታ ነው፡፡

ይህ መሰረታዊ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ  አልፎ አልፎ ጠባብነት የተጠናወታቸው ጥቂት የህብረተሰብ ክፍሎች በክልላቸው ውስጥ በሚኖሩ የሌሎች ብሄር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ የሚያደርጉበት አጋጣሚም መፈጠሩ የማይካድና የዴሞክራሲው ለጋ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚጠበቅ ነው፡፡ይህም አንድ ትምክህተኛ የተናገረውን የተሳሳተ ሃሳብ ወይም ጥቂቶች ያንጸባረቁትን የንቀት አስተሳሰብ መነሻ በማድረግ በሌላ ብሄር ተወላጆች ላይ በተከፈቱና በምናስታውሳቸው የጥቃትና የማጥላላት ዘመቻዎች የሚረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ሁነት በአካባቢ ልጆች የተዋቀረው አስተዳደር /አመራር/ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተልዕኮውን በአግባቡ መወጣት ሲሳነው በሌሎች ህዝቦች ላይ በከፈታቸው የማጥላላትና የማጥቃት ዘመቻም የተረጋገጠ ነው፡፡

ምን ይህን ብቻ በሙስና ተዘፍቆ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ተግባራትን ባለመፈጸሙ የተቀሰቀሰውን የህዝብ ቅሬታ ከሌሎች ክልሎች በመጡ ተወላጆች ላይ ባነጣጠረ ዘመቻ አቅጣጫ ለማስቀየር በመሞከርም መገለጹ እውነትና የማይተባባል ሃቅ ነው፡፡
ይህና በጥቂቶች ሊገለጽ የቻለው አጋጣሚ ደግሞ በምርጫ 97 የከሰመ ሊመስለንና እንደገና ለደረጀው የትምክህት ሃይሉ በፖለቲካ ፓርቲ ስም እና በግል ሚዲያ ስም ለሚጫወታቸው የአንድን ወገን የበላይነት ዓላማ ያደረገ ቁማር ጥሩ እድል እንደፈጠረለት ባለፉት ዓመታት ብቻ መኢአድና አንድነት እንደ ፓርቲ አመራሮቻቸው ደግሞ እንደመሪ ያወጧቸው መግለጫዎችንና ለዚሁ አላማ በሚሰሩ ጋዜጦች ላይ ያሰፈሯቸውን መጣጥፎች በማየት ማረጋገጥ የሚቻል ነው፡፡

እነዚህን መግላጫዎችና መጣጥፎች ወደኋላ ተመልሰን ብናይ ከላይ በተመለከተውና በጥቂቶች የሚገለጸውን የግጭት ፣ መፈናቀልና አለመግባባቶች እጅግ አብዛኛውን  ጊዜ ከትክክለኛ መጠናቸው አግዝፈው በማቅረብ ስርዓቱ ህዝቦች ተስማምተው ሊኖሩ የማይችሉበት እንደሆነ ለማስመሰል የሞከሩባቸውን እውነታዎች የምናገኝ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ከላይ በተመለከተው የጥቂቶች መነሻ በደቡብ ክልል ጉራ ፈርጻ የተፈጠረውን አለመግባባትና መፈናቀል መኢአድና አንድነት ስርዓቱ ለአማራው ህዝብ ያልተመቸ በማስመሰል ሰፊው የአማራ ህዝብ በራሱ ስርዓት ላይ ጥላቻ እንዲኖረው መልፋታቸውና አሁንም እየቀጠሉበት መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታና አሁንም በእነዚሁ ሃይሎች እየተራገበ የሚገኝ ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህና በተቃውሞ ፖለቲካ ስም የተሰባሰቡ መኢአድና አንድነት የተሰኙ ፓርቲዎች በሌሎች ክልሎች አንዲት ትንሽ ችግር ስትፈጠር በአፋዊ እንደሚያወሩት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ በዴሞክራሲያዊና ህገ መንግስታዊ መንገድ እንዲፈታ ከማድረግ ይልቅ በፍጥነት ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ አጋጣሚ አድርገው መጠቀማቸውም ሆነ ይህንኑ መንገድ እየቀጠሉበት መሆኑ የማይስተባባል ሃቅ ነው፡፡ ሠሰማያዊም የአንድነት ፍንካች ነውና ለትምክህት ፍላጎቱ የሚጠላቸውን ብሄር ተኮር ፓርቲዎች ሰብስቦ ህገወጥ ሰልፍ ማድረጉና ሰልፉን ተከትሎ የተወሰደበት እርምጃን በተመለከተ መነታረክ የጀመረው ከላይ በተመለከቱትና በዋናነት መኢአድና አንድነት ከተጠቀሙበት ጸረ ዲሞክራሲያዊ መንገድ መነሾነት ነው፡፡ በእነዚህ ሃይሎች የሚመሩትና ለአንድ ብሄር የበላይነት የሚተጉት ግን ደግሞ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ህገ መንግስታዊ መብት የሰጣቸውን ሥርዓት ከለላ አድርገው በግል ሚዲያ ስም የተቋቋሙት ጋዜጦችም በቀላሉ በቁጥጥር ስር ሊውል የሚችለውን እና የሚገባን ችግር እንደ ሰለጠነ እና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው አንድ አካል ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ ከማመላከት ይልቅ በላይ በላይ እያራገቡ የማይበርድ የህዝብ ለህዝብ ግጭት ለመፍጠር መራወጣቸውም የነበረና አሁንም የሰማያዊን ሰልፍና ያመጣውን ጣጣ ተከትሎ በሰሯቸው ከላይ የተመለከቱ ጸረ ዲሞክራሲያዊ እና መርህ የለሽ ዘገባዎች ማረጋገጥ የሚቻል ይሆናል፡፡

ሥርዓቱ ፈጠረላቸውን የመደራጀት መብትና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ከለላ በማድረግ ለትምክህት አስተሳሰባቸው እየተገለገሉበት የሚገኙት መኢአድ አንድነትና ሰማያዊ የተሰኙ ፓርዎችን ጨምሮ በእነርሱ የሚነዱ ትምክህት ወለድ ሚዲያዎችና የውጭ ኒዮ ሊበራሊስት አራማጅ ሚዲያዎች ሰብአዊ መብት አስጠባቂ በሚል ስም ከተቋቋመው

አክራሪ ሃይሎች ጋር ጥምረት ፈጥረው በቅርብ ጊዜ በኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰውን ሁከት እንዴት መጠቀሚያ ያደረጉት መሆኑን በማስታወስ ጉዳዩን በሚገባ ማብላላት ይቻላል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በተቀሰቀሰው ሁከት አንዳንድ የጠባብነት አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ሰዎች በአማራ ተወላጆች ላይ የፈጸሙትን ያልተገባ ጥቃት መላው የኦሮም ህዝብ የፈጸመው በማስመሰል የህዝብ ለህዝብ ግጭት ለመቀስቀስ ያልፈነቀሉት ድንጋይ እንዳልነበር እና ግን ደግሞ ከላይ በተመለከተው አግባብ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ስር ከመስደዱ ጋር ተያይዞ መክሸፉን ማንም የማይክደውና የስብስቡን ግብ የሚያመላክት ሁነኛና ለምርጫ 2007 የታለመ የቅርብ ጊዜ አስረጅ ነው፡፡ሥርዓቱ ስር ከመስደዱ ጋር ተያይዞ ብዙሃኑ የኦሮሞ ህዝብ በዚህ ቅጽበታዊ ችግር ለጥቃት የተጋለጡ የአማራ ተወላጆችን አቅፎና ደግፎ ብቻ ሳይሆን ከማንኛውም ጥቃት ተከላክሎ ጠብቋቸው እያለ ይህን አኩሪ የህዝብ ባህሪ ደፍቀው የጥቂት ብልሹ ሰዎችን መጥፎ ድርጊት በመግለጫ ጋጋታና በመጣጥፎች አጋነው በማቅረብ የተገለጹትን ሠማያዊ መኢአድና አንድነት የማንዘነገና የሰሞኑ መንገድም የዚሁ ተቀጽላ መሆኑን የሚያረጋግጥልን ማሳያ ነው፡፡

ይህ ያልበቃቸው እነ ሠማያዊ እና መኢአድ  እንዲሁም አንድነት በተለይ በአማራ ክልል ውስጥ በሰላም እየተማሩ በሚገኙ የሌሎች ብሄር ተወላጆች ላይ ተመሳሳይ የበቀል እርምጃ እንዲወሰድ ከኒዮ ሊበራል ሚዲያውና በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም ከተቋቋሙ ተቋማት ጋር በጥምረት ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸውም የማይረሳና የቅርብ ጊዜ የትምክህት ሃይሉ እውነታ ነው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ለአንድ ብሄር የበላይነት መትጋታቸው ህሊናቸውን እንኳ ሳይከነክናቸው ዛሬም እንደ ትናንቱና እነርሱም የሚታትሩለት አንድ ብሄር የበላይነት ያለ በማመሰል ፖለቲካቸውም ይታወቃሉ፡፡የስልጣን ደረጃዎችን እና ማዕረጎችን እየቆጠሩና እየቆነጠሩ በልሳኖቻቸውና ለአክራሪው ሚዲያ ማስተጋባታቸው ያለና የሚገለጡበት ሌላው እውነታ ነው፡፡

አንድ ምሳሌ እንጨምር፡- በቅርቡ በአማራ ክልል አንድ የስልጠና መድረክ ላይ የትምክህት አስተሳሰብ የአማራ ህዝብን መብትና ጥቅም በመጉዳት ስላደረሰው በደል የተሰጠውን ማብራሪያ ተከትሎ ይህን የማጋለጥ ስራ ባከናወኑት  አንድ የብአዴን መሪ ላይ

‹‹የአማራ ህዝብን ስለዘለፈ ለፍርድ ይቅረብልን›› የማለት ዘመቻ በመክፈት መኢአድ አንድነትና ሰማያዊን የቀዳማቸው ያልነበረ መሆኑን ስናስታወስ ፤ይህ ሁሉ በሰለማዊ ሰልፍ ስም የሚደረግ ግርግር ግቡ አዲሱን ወይን በማይቻለው አሮጌ አቁማዳ ለመክተት የሚደረግ ጥረት ስለመሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የትምክህቱ ሃይል መገለጫ የሆኑትን እና በተግባር ስለ አንድ ብሄር የበላይነት እየሰሩ ስለመሆናቸው ከላይ በተመለከተው አግባብ ለሚታወቁቱ ሠማያዊ አንድነትና መኢአድ ፓርቲዎች ስለ አንድ ብሄር በላይነት በተቃውሞ ፖለቲካ ስም እየተጉ እና ያለፈውን አስከፊ ሥርዓት ለመመለስ እየናፈቁ መሆናቸውን እነርሱም ከላይ በተመለከተው አግባብ ተገልጠው በብሄር የተደራጁትም እና በተለይ የመድረኩ አባል ፓርቲዎችም በተጨባጭ ያረጋገጧቸው ሃቆችና ያለመግባባታቸውም መነሻ መሆኑን በተጨባጭ የመሰከሩባቸው የበዙ እውነታዎችን አይተናል።ይህ ባለበት ሁኔታ ከሰሞኑ ምርጫ 2007ን ታሳቢ አድርገው እነ ሰማያዊ ለትምክህት አስተሳሰባቸው ስለበላይነት ላደረጉት ህገወጥ ጥረት የተወሰደውን እርምጃ በመኮነን አንድነትንና መኢአድን አንካሳ ዶሮም ያልቀደማቸው እንደሆነ ከላይ በተመለከተውና ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ከሰፈረው ዘገባ ማረጋገጥ ተችሏል። በተመሳሳይም መድረክ እና አባል ፓርቲዎቹም እርምጃውን ለመኮነንያበቃቸው መነሻ የአማራጭ ፕሮግራም እጦታቸው ምትክ የሆናቸው የጠባብነት አስተሳባቸው እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡ ግምታችንንም በሁነኛ አስረጂዎች እያንሰላሰልን እርስ በራሳቸው ከሚሰጧቸውም ፍረጃዎች ጋራ እያጋመድን ምርጫ 2007ን ታሳቢ ያደረጉ የሠላማዊ ሰልፍ ግቦችን ግና በሚገባ እንተርካለን፡፡